ምንባብ

ኢትዮጵያ በብዙ ታሪክ ፀሐፊዎች የተደነቀች ረጅምና አኩሪ ታሪክ ያላት ሀገር ናት። ታዋቂነት ያላት ሀገራችን በዘመናት ታሪኳ ውስጥ ብዙ ውጣ ውረድና ፈተና ደርሶባታል። ይሁን እንጅ በአባቶቻችንና በእናቶቻችን ያልተቋረጠ ተጋድሎ ህልውናው ተጠብቆ ኖሯል።

በጀግንነትና በመስዋዕትነት ያጌጠው የኢትዮጵያ ነፃነት ታሪክ ተከብሮ መኖር ሲወሳ ምንጊዜም መዘንጋት የሌለበት ጉዳይ ሁኔታው የድል ወይም ያጋጣሚ ሳይሆን የሰፊው ህዝብ ጀግንነትና መስዋዕትነት ውጤት መሆኑ ነው። ኢትዮጵያ በረዥም ታሪኳ ውስጥ ያለፈቻቸው ተጋድሎ የተሟሉ ተጋድሎዎች ሁሉ ነፃነቷንና ሉአላዊነቷን ለመጠበቅ እንጅ የሌሎችን ግዛትና አንድነት ለመድፈር አይደለም። የሌሎችን ያለመመኘቷን ያህል ግን ሌሎች እጃቸውን አልሰበሰቡም። ሀገራችን የጠላቶቹን አላማ ካደረጓት ልዩ ልዩ ምክንያቶች መካከል አንዱ የተፈጥሮ ሀብቷና ውበቷ ሲሆን ሌላው ደግሞ የምትገኝበት አካባቢ ነው።

ኢትዮጵያ በአባይ ሸለቆ መካከል ቁልፍ ስፍራ ይዛ ትገኛለች። የውጭ ሀይሎች ያለማቋረጥ ሲነሱብን የኖሩትም ይህንን አንዱን መሰረታዊ ምክንያታዊ ሁኔታ ምክንያት በማድረግ ለመቆጣጠር በመፈለግ እንደሆነ ይታወቃል። ይሁን እንጅ ለሀገራችን ያለንን እጅግ ጥልቅ ፍቅር ምርኩዝ በማድረግ የውጭ ሀይሎች ያልተቋረጠ ጠላትነትና ወረራ ተቋቁመናል በመቋቋም ላይም እንገኛለን የተሰነዘሩብን ተደጋጋሚ ጥቃቶች የቁጭትና ያትንኩኝነት መንፈሳችንን አጠናከሩት እንጅ እንድንበረግግ አላደረጉንም። ስለዚህ በተደጋጋሚ የተቀናጀናቸው ድሎች ምስጥር ናቸው።

ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ከምንባብ የወጡ ናቸው። በምንባቡ መሰረት ከተሰጡት አማራጮች መካከል ተስማሚውን ፊደል ምረጡ።

________1/ ኢትዮጵያ በአባይ ሸለቆ __________ ቦታ ይዛለች

ሀ. አላስፈላጊ ለ. ወሳኝ ሐ. የማይጠቅም መ. ሁሉም

________2/ ተደጋጋሚ ጥቃቶች ምን ፈጠሩብን?

ሀ. ቁጭት ለ. አትንኩኝ ባይነት ሐ. ምንም መ. ሀና ለ መልስ ነው

________3/ ኢትዮጵያ በብዙ ታሪክ ፀሐፊዎች ምን ዓይነት ሀገር ነች?

ሀ. አኩሪ ታሪክ የሌላት ለ. አኩሪ ታሪክ ያላት ሐ. ሀ ና ለ መ. ሁሉም

________ 4/ ምንባቡ ስንት አንቀጽ አሉት?

ሀ. አንድ ለ. አራት ሐ. አምስት መ. መልሱ አልተሰጠም

________5/ የኢትዮጵያ ታሪክ ያጌጠው በ ____________________ ነው።

ሀ. በጀግንነት ለ. በመስዋዕትነት ሐ. በነፃነት መ. ሁሉም

________6/ ሀገራችን የሌሎችን ሀገሮች ሉአላዊነት

ሀ. ትደፍራለች ለ. አትነካም ሐ. ትተነኩሳለች መ. ሁሉም

_______7/ ኢትዮጵያን የጠላቶቿ አላማ ያደረጋት

ሀ. አቀማመጧ ለ. የተፈጥሮ ውብቷ ሐ. ሀና ለ መ. መልሱ አልተሰጠም

_______8/ ኢትዮጵያ የሌሎችን ሀገራት ሀብት

ሀ. አትመኝም ለ. ትመቀኛለች ሐ. ትቀናለች መ. ትነካለች

_______9/ አባቶቻችንና እናቶቻችን

ሀ. ጀግና ናቸው ለ. አትንኩኝ ባይ ናቸው ሐ. ሀገራቸውን ይወዳሉ መ. ሁሉም

_______1 0. ፀሐፊው ድል ሲል _____________________ ማለቱ ነው

ሀ. ማሸነፍ ሐ. መሸነፍ ሐ. መረበሽ መ. ማብሰር

<u>ከዚህ ቀጥሎ ለቀረበው ፈሊጣዊ አነጋገር ተመሳሳይ የሚሆነውን መልስ ምረጡ</u>

_______11/ ሰማይ ተደፋበት

ሀ. በጣም አመመው ለ. ግራ ገባው ሐ. አጭር ሆነ መ. ረዥም ሆነ

_______12/ ሸርካታ

ሀ. ውሸታም ለ. ተናዳጅ ሐ. ጉበዝ መ. ሰነፍ

_______13/ ስማ በለው

ሀ. አዋጅ ለ. አስታወሰ ሐ. አስታወሰው መ. ሁሉም

_______14/ ሲበሉ የላኩት

ሀ. ችኩል ለ. ተናዳጅ ሐ. ሆዳም መ. ሁሉም

_______15/ ቅቤ ጠባሽ

ሀ. እወደድ ባይ ለ. ሞኝ ሐ. ሚያታልል መ. መልሱ አልተሰጠም

_______16/ ተርብ ነው

ሀ. ጉበዝ ነው ለ. ሰነፍ ነው ሐ. ስራ አይወድም መ. ሁሉም

_______17/ ታረሰች

ሀ. ወልዳ እንክብካቤ ተደረገላት ሐ. ሀ ና ለ

ለ. አልወለደችም መ. ሁሉም

________18/ ቹበቹበ

ሀ. በርካሽ ሸጠ ለ. አልሸጥ አለ ሐ. ተናደደ መ. መልሱ አለተሰጠም

________19/ ባላንጣ

ሀ. ጠላት ለ. ባለንብረት ሐ. ባለቤት መ. ባለንብረት

________2 0/ ሳር ቅጠሉ

ሀ. ሁሉም ለ. አንዳንድ ሰው ሐ. ብዙ ጊዜ መ. አንዳንድ ጊዜ

<u>ከዚህ በታች የቀረቡትን እሳሌያዊ አነጋገሮች ሊያሟሉ የሚችሉ ሀረጎችን ምረጡ</u>

________21/ ሁሉ ያልፋል ________________________

ሀ. ግን ያበሳጫል ለ. እስኪያልፍ ያለፋል ሐ. ለጊዜው ያሰንፋል መ. ሁሉም

________22/ __________________ማጭድ አታውሰው

ሀ. ሆድ ለባሰው ለ. ለተደሰተ ሐ. ለተገረመ መ. ለሚያሾፍ

________23/ ሌባ ላመሉ __________

ሀ. ይናደዳል ለ. ዳቦ ይልሳል ሐ. አይሰርቅም መ. ተመልሶ ይመጣል

________24/ ላም ባልዋለበት

ሀ. ኩበት ለቀማ ለ. ወተት የለም ሐ. ጥጃዋ ጠፋች መ. ሳር አይገኝም

________25/ ልጅ ለናቷ

ሀ. ልብስ ገዛች ለ. ምጥ አስተማረች ሐ. ጥሩ ነች መ. ሁሉም

________26/ ማር ሲበዛ

ሀ. ይጣፍጣል ለ. ይመራል ሐ. ጥሩ ነው መ. ይጎመዝዛል

________27/ እሩቅ አሳቢ

ሀ. ቅርብ አዳሪ ለ. ረዥም ይጓዛል ሐ. አስተዋይ ነው መ. መልሱ አልተሰጠም

________28/ ሰማይ ይወድቃል ብሎ

ሀ. ፀሎት ጀመረ ለ. ባላ ተከለ ሐ. ማልቀስ ጀመረ መ. ተበሳጨ

_______29/ ሰነፍ አረኛ

ሀ. መጠበቅ አይወድም　　ለ. ከሩቅ ይመልሳል　　ሐ. ከብቶች ጠፉበት　　መ. ሁሉም

_______30/ ሰው አላገር

ሀ. መሬት አለዘር　　ለ. ይኖራል　　ሐ. ሄደ ባላገር　　መ. ኖረ ሲደናገር

<u>ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒ የሆነውን መልስ ምረጡ</u>

_______31/ ሀሩር

ሀ. ብርድ　　ለ. ሙቀት　　ሐ. በረሃ　　መ. ቆላ

_______32/ ነሲብ

ሀ. ዕድል　　ለ. መላ　　ሐ. ግምት　　መ. ብልሀት

_______33/ ገልቱ

ሀ. ብልህ　　ለ. ሥልጡን　　ሐ. ጨሰ　　መ. ሞኝ

_______34/ ቁባት

ሀ. ውሽማ　　ለ. ጭን ገረድ　　ሐ. ቅምጥ　　መ. ሚስት

_______35/ በዓል

ሀ. የደስታ ቀን　　ለ. የአዘቦት ቀን　　ሐ. የሀዘን ቀን　　መ. ሁሉም

_______36/ አተካሮ

ሀ. ንዝንዝ　　ለ. ረብሻ　　ሐ. ጭቅጭቅ　　መ. ሰላም

_______37/ ደማቅ

ሀ. የማይታይ　　ለ. አይነ ግብ　　ሐ. ፈዛዛ　　መ. ሁሉም

_______38/ ነጋ

ሀ. ብርሃን ሆነ　　ለ. ታየ　　ሐ. ጨለመ　　መ. ሁሉም

_______39/ ደምፍላት

ሀ. ንዴት　　ለ. ትዕግስት　　ሐ. መረበሽ　　መ. ማዘን

_______40/ ኩርማን

ሀ. ትልቅ ለ. ትንሽ ሐ. መጠነኛ መ. መሀከለኛ

<u>ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ የሚሆነውን ፊደል ምረጡ</u>

_______41/ ፀጋ

ሀ. ስጦታ ለ. ክብር ሐ. ንዴት መ. ሀሳብ

_______42/ ደመኛ

ሀ. ወዳጅ ለ. ጠላት ሐ. ባላንጣ መ. መንገደኛ

_______43/ ሸነገለ

ሀ. አመሰገነ ለ. አታለለ ሐ. አሞኘ መ. ለ ና ሐ

_______44/ ጥንድ

ሀ. ጥምር ለ. ነጠላ ሐ. ለብቻ መ. ሀናለ

_______45/ ገናና

ሀ. ታዋቂ ለ. አርቲስት ሐ. ተዋናይ መ. ለ ና ሐ

_______46/ ዲታ

ሀ. ሀብታም ለ. ደሀ ሐ. የመንግስት ሰራተኛ መ. ምንም የሌለው

_______47/ ዋዜማ

ሀ. መዳረሻ ለ. ትናንት ሐ. ያለፈ ቀን መ. ድራማ

_______49/ ከነፈ

ሀ. በረረ ለ. ቀስ አለ ሐ. መላክ ሆነ መ. ሁሉም

_______5ፀ/ ወቀሰ

ሀ. ነቀፈ ለ. አሞገሰ ሐ. አስታወሰ መ. አታለለ

ቀጥሎ የቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛ ምላሽ ምረጡ

_______51/ ከሚከተሉት ዐ.ነገሮች ትክክለኛ የትኛው ነው?

ሀ. አስር ብሮች አሉኝ ሐ. አስር ብር አለኝ

ለ. አስሮች ብሮች አሉች መ. ሁሉም

_______52/ አልበላም ለሚለው ቃል ስርወ ቃል የቱ ነው?

ሀ. በላ ለ. እየበላሁ ሐ. ልበላ መ. ባልበላስ

_______53/ አበላ ለሚለው መነሻ ቅጥያው ቃሉ የቱ ነው?

ሀ. አ ለ. በ- ሐ. -ላ መ. መልሱ አልተሰጠም

_______54/ ካህናት በሚለው ቃል የብዙ ቁጥር አመልካች ቅጥያው _________ ነው

ሀ. ናት ለ. አት ሐ. ት መ. ኣት

_______55/ ቤት የሚለው ቃል __________________ ነው

ሀ. ነፃ ምዕላድ ለ. በቂ ምዕላድ ሐ. ጥገኛ ምዕላድ መ. ሁሉም

_______56/ ከሚከተሉት ውስጥ የቃል ክፍል ያልሆነው

ሀ. ስም ለ. ግስ ሐ. ቅጽል መ. መልሱ አልተሰጠም

_______57/ ከሚከተሉት መስተዋድድ ቃል የትኛው ነው?

ሀ. መፀሀፍ ለ. ነው ሐ. እሱ መ. ወደ

_______58/ ከሚከተሉት ውስጥ መቀበያ ክሂል ያልሆነው የቱ ነው ?

ሀ. መናገር ለ. ማውራት ሐ. መፃፍ መ. ሁሉም

_______59/ ከሚከተሉት ውስጥ ልብ ወለድ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ከአድማስ ባሻገር ሐ. የኢትዮጵያ ታሪክ

ለ. ፍቅር እስከመቃብር መ. እሮማይ

_______ 6 0/ የልብ ወለድ አለባዊያን ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ትልም ለ. ታሪክ ሐ. መቼት መ. መልሱ አልተሰጠም